**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በአካል ተመልሰው ለማስተማር የጤና አጠባበቅ ጥንቃቄ መረብ አዘጋጅቷል፣ ዳግም የመከፈት እቅዶችን ኖቬምበር 6 እና 10 ለትምህርት ቦርድ ያቀርባል**

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በአካል ተመልሰው ለማስተማር የጤና አጠባበቅ ጥንቃቄ መረብ አዘጋጅቷል። የጤና አጠባበቅ ጥንቃቄ መረቡ ከ CDC መመሪያ ጋር የሚጣጣም ሲሆን የተዘጋጀውም ከሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና ኃላፊዎች ጋር በመመካከር ነው።

በጁላይ ወር፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በአንደኛው ሴሚስተር ዲስትሪክቱ በቨርቹወል ሞዴል ብቻ እንደሚሠራ እና በኖቬምበር ውሳኔው እንደገና እንደሚገመገም ለሠራተኞች እና ቤተሰቦች ተገልጾ እንደነበር ይታወቃል። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሠራተኞች ስለ ሁለተኛው ሴሚስተር እንደገና የመከፈት ሁኔታ እና የጤና አጠባበቅ ጥንቃቄን መሠረት በማድረግ ከዚያም ቀደም ብሎ ለመከፈት የሚያስችል ሁኔታ የሚኖር ከሆነ ውይይት ለማድረግ እና አስተያየት ለመስጠት ኖቬምበር 6 እና ኖቬምበር 10 ወደ ትምህርት ቦርድ ይመለሳሉ። በንድፍ ደረጃ የቀረቡትን እቅዶች ለወላጆች፣ ለተማሪዎች እና ለሠራተኞች እናጋራለን።

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሁሉም ተማሪዎች በቨርቹወል ሞዴል ጥራት ያለው ትምህርት እንዲቀስሙ ለማድረግ በቁርጠኝነት እየሠራ ነው። ዲስትሪክቱ የመማር ማስተማር ክፍተቶች እንዳሉ በመገንዘብ፣ ለተማሪዎች ውጤታማነት እንቅፋት የሚሆኑ ምክንያቶችን ለመቅረፍ የሚያስችሉ በርካታ እርምጃዎችን በመውሰድ ላይ ይገኛል፤ ተጨማሪ የሙያ ማዳበር ዕድሎችን ለሠራተኞች መስጠት፣ የተማሪዎችን ፍላጎት ለማሟላት ሥርዓተ ትምህርቱን ማሻሻልና ከትምህርት ቤት በፊትም ሆነ ከትምህርት ቤት በኋላ በማጠናከሪያ ትምህርት የማስጠናት ድጋፍ ፕሮግራሞችን ይሰጣል። ስለነዚህ ጥረቶች የበለጠ ለማወቅ አክቶበር 27 የትምህርት ቦርድ ስብሰባ ይመልከቱ።

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በድጋሚ ለመክፈት በምናደርገው ጥረት የጤንነት ጥንቃቄን ቅድሚያ ትኩረት በመስጠት ከትምህርት ቦርድ፣ ከሠራተኞች እና ከማህበረሰቡ ጋር በጋራ መሥራታችንን እንቀጥላለን።

**የኤለመንተሪ ትምህርት ቤት መርሃግብር ለውጦች ኖቬምበር 11 ይፋ ይሆናሉ**

አክቶበር 27 በተካሄደው የትምህርት ቦርድ ስብሰባ ወቅት፣ የ MCPS ባልደረቦች በኤለመንተሪ ትምህርት ቤት መርሃግብር ላይ መደረግ ያለባቸውን ለውጦች አቅርበዋል። እነዚህ ለውጦች የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎችን የጠዋት ክፍለጊዜ መርሃግብር የሚመለከቱ ሲሆን ረቡዕ፥ ከኖቬምበር 11 (ሁለተኛው የማርክ መስጫ ክፍለጊዜ የሚጀመርበት ወቅት) ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናሉ። እነዚህ ለውጦች የተደረጉት ስለስክሪን ዕይታ ሰዓት፣ የማስተማሪያ ብሎኮች እና የአስተማሪ ዕቅድን በሚመለከት ዲስትሪክቱ ከሠራተኞች እና ከቤተሰቦች ለተገኘው ግብረ መልስ ምላሽ ለመስጠት ነው። ይህ የመርሃግብር ክለሳ የተደረገበት ዓላማና ግብ የስክሪን ጊዜን በመቀነስ፣ ስፔሻል ኢጁኬሽን ለሚማሩ ወይም ተዛማጅ አገልግሎት ለሚያገኙ ተማሪዎች በራሳቸው ጥረት እንዲሠሩ ወይም በአነስተኛ ቡድን እየሠሩ የቤት ሥራዎቻቸውን የሚያጠናቅቁበት ተመጣጣኝ ጊዜ ለመስጠት ነው።

የለውጦቹ ማጠቃለያ ከዚህ በታች ይገኛል፦

- በኤለመንተሪ መርሃግብር ላይ የተደረጉት ክለሳዎች የሚነኩት እሮብ ጠዋትን ብቻ ነው። ከ 9-11:30 am. የትምህርት ብሎክ እሮብ ከሠዓት በኋላ ላይ ምንም ለውጥ አልተደረገም።
- ሁሉም ተማሪዎች በየሳምንቱ ረቡዕ ከጠዋቱ 9 a.m ላይ የሚጀምሩ ሲሆን ለ30 ደቂቃ በሚቆየው የክፍል ስብሰባ ከአስተማሪዎቻቸው ጋር ይገናኛሉ።
- ረቡዕ ጧት ሁለት የትምህርት ብሎኮች (blocks) ይኖራሉ። ብሎክ #1 የትምህርት ክፍል ስብሰባ በቀጣይነት የሚካሄድ ሲሆን ከ 9:30-10:15 a.m. ይካሄዳል። በዚህ ጊዜ፣ ተማሪዎች በተናጠል ይሠራሉ፣ ከአስተማሪዎቻቸው ጋር ይሠራሉ፣ ካልሆነም ድጋፍ ወይም የተለያየ አገልግሎት ያገኛሉ።

- በ 10:15 a.m. ለመዝጊያ እና በብሎክ #2 ወቅት ምን መሥራት እንደሚኖርባቸው መግለጫ ለማግኘት በጠቅላላ ከክፍል ተማሪዎች እና ከአስተማሪ ጋር እንደገና ይገናኛሉ።
- ብሎክ #2 የሚካሄደው 10:30-11:30 a.m. ነው። በሁለተኛው ብሎክ፣ ተማሪዎች በራሳቸው ጥረት በተናጠል በሚሠሩት ሥራ ወይም ከረዳት አስተማሪዎች እና ተዛማጅ አገልግሎት ሰጪዎች ጋር በሚሠሩት ሥራ ይጠመዳሉ።
- የምሳ እና የጤና እንቅስቃሴ የመናፈሻ እረፍት ከ 11:30 a.m.-1 p.m. ይሆናል።
- የረቡዕ ጠዋት ብሎኮች ከእንግሊዝ ወዲያ ቤንችማርክ ሊተረሲ እና ኡርካ ሂሳብ (Benchmark Literacy and Eureka Math) ላይ አያተኩሩም። ይልቁንም ተማሪዎች ተዛማጅ ይዘት ያለው ድጋፍ በማግኘት፣ ክለሳ በማድረግ እና እውቀት ማዳበር በሚችሉባቸው እድሎች ይቀጥላሉ።
- ሰኞ፣ ማክሰኞ፣ ሐሙስ፣ ዓርብ እንዲሁም ረቡዕ ከሰዓት በኋላ የሚደረጉ ፕሮግራሞች ሳይለወጡ ይቀጥላሉ።

ተማሪዎች በእያንዳንዱ ብሎክ ማጠናቀቅ የሚጠበቅባቸው የትምህርት ተግባሮችን በሚመለከት ትምህርት ቤቶች ከወላጆች ጋር ይገናኛሉ። እባክዎ ረቡዕ፣ ኖቬምበር 11 ጀምሮ ምን እንደሚደረግ ዝርዝር ነገሮችን ለማወቅ ኖቬምበር 9 በሚውልበት ሰምን ከእርስዎ ልጅ ትምህርት ቤት የሚላክ ኢ-ሜይል ይመልከቱ።

**ESOL ቨርቹወል ታወንሆል ስብሰባ ኖቬምበር 4 ይካሄዳል።**

**<Story:>**በትምህርት ቦርድ የልዩ ህብረተሰብ ኮሚቴ እንግሊዝኛ ለሌላ ቋንቋ ተናጋሪዎች ማህበረሰብ (ESOL) ቨርቹወል የውይይት መድረክ ያካሄዳል። የመድረኩ ዓላማ ለ ESOL ተማሪዎች ወሳኝነት ያላቸው መረጃዎችንና ድጋፎችን ለማጋራት ነው። መድረኩ የተዘጋጀው ለረቡዕ፣ ኖቬምበር 4 ከ 4 - 6 p.m. ነው። ኮሚቴው ከእናንተ ለመስማት የሚፈልግ ስለሆነ፣ እባክዎ ጥያቄዎችን በዚህ ድረ-ገጽ ላይ በቅድሚያ ያቅርቡ፡- http://www.MCPSSubmitQuestion.org. ጥያቄዎችን የማቅረቢያ ቀነገደብ ሰኞ፣ ኖቬምበር 3 እስከ 5 p.m. ሲሆን ፕሮግራሙ በእንግሊዝኛ እና በስፓንሽ ቋንቋ በ MCPS-TV፣ Condado TV፣ በ MCPS ድረ-ገጽ እና YouTube ላይ ይተላለፋል። በነዚህ ድረ-ገጾች ላይም ይቀርባል፡- www.youtube.com/mcpstvእናwww.youtube.com/mcpstvespanol

**የትምህርት ቦርድ ስለ ካፒታል ማሻሻያ ፕሮግራም እና የማካለል ጥናት ህዝባዊ አስተያየትና ውይይት ለማድረግ ስብሰባ ያካሄዳል**

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ስለበጀት ዓመት (FY) 2022 የካፒታል በጀት፣ ስለ 2021-2026 የካፒታል ፕሮግራሞች ማሻሻያ (CIP) እና በኖቬምበር ወር የሰመርሴትና ዌስትብሩክ (Somerset and Westbrook) የማካለል ጥናት ላይ በርካታ የሕዝብ አስተያየት መቀበያ ስብሰባዎችን ያካሂዳል። የህዝብ አስተያየት ለመቀበል በሙሉ በቨርቹወል ይካሄዳል። ምስክርነት ለመስጠት በጽሑፍ ወይም በቅድሚያ-ሪኮርድ የተደረጉ የቪዲዮ/የድምጽ ቅርጾቶች ተቀባይነት ይኖረዋል።

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ሱፐርኢንተንደንት ጃክ ስሚዝ (Montgomery County Public Schools Superintendent Jack R. Smith) ለበጀት ዓመት 2022 የተነደፈ የካፒታል በጀት፣ ለበጀት ዓመት 2021 - 2026 CIP ማሻሻያዎችን እና የሠመርሴት (Somerset) እና ዌስትብሩክ (Westbrook) የማካለል ጥናት አክቶበር 26/2020 አቅርበዋል።

ህዝባዊ አስተያየቶች በሚከተለው መርሃግብር መሠረት ይከናወናሉ፡-

| ህዝባዊ አስተያየቶችን መቀበያ ቀን | የምሥክርነት ርእሶች |
|---|---|
| ኖቬምበር 2/2020, 6 p.m. | አጠቃላይ የ CIP ምስክርነት እና ከሰመርሴትና ዌስትብሩክ (Somerset and Westbrook) ምሥክርነት ጋር የተያያዘ የማካለል ጥናት |

| | |
|---|---|
| ኖቬምበር 5/2020, 6 p.m. | አጠቃላይ CIP ምስክርነት |

ግብዓት ማቅረብ የሚፈልጉ ግለሰቦች በኢንተርኔት አማካኝነት መመዝገብ ይችላሉ። ይበልጥ መረጃ እዚህ ድረ-ገጽ ላይ ይገኛል፦ https://www.montgomeryschoolsmd.org/boe/community/participation.aspx

የትምህርት ቦርድ ስለ CIP የመጀመሪያውን የሥራ ክፍለጊዜ ሰኞ፣ ኦክቶበር 26 አካሂዷል። ሁለተኛው የሥራ ክፍለጊዜ ሐሙስ፣ ኦክቶበር 29 በ 10 a.m. ተካሄዷል። CIP ለማጽደቅ በጊዜያዊነት የተያዘው ቀነ ቀጠሮ ሐሙስ፣ ኖቬምበር 19 በ 5:30 p.m. ይሆናል።

**ለሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ተከታታይ "Let's Talk Careers Speaker Series" ይከፈታል**

የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤትና የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን በሙሉ መጥራት!
የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) "Let's Talk Careers" የተሰኘ በጤና እንክብካቤ፣ በንግድ ሥራ፣ እና ምህንድስና በመሣሰሉት የሙያ ተሞክሯቸውን በሚያጋሩ የ MCPS የቀድሞ ምሩቃን በየወሩ በቀጥታ የሚተላለፍ ተከታታይ ንግግር የሚደረግበት ፕሮግራም ይጀመራል። የመጀመሪያው ረቡዕ፣ ኖቬምበር 18 ከ 10–11:30 a.m. የሚካሄድ ሲሆን የ CAVA ተባባሪ መስራቾች Ted Xenohristos፣ Ike Grigoropoulos እና Dimitri Moshovitis ላይ ያተኩራል።

ተማሪዎች ከስብሰባው ቀን አስቀድመው ጥያቄዎችን እዚህ ላይ እና በ "YouTube chat" በቀጥታ ማቅረብ ይችላሉ።

እዚህ ወይም በ MCPS-TV (Comcast 34፣ Verizon 36 እና RCN 89) ይመልከቱ።

Let's Talk Careers

**ስለ MCPS አትሌቲክስ ወቅታዊ መግለጫ**

ኦክቶበር 26፣ የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ቦርድ በሜሪላንድ ሁለተኛ ደረጃ የህዝብ ትምህርት ቤቶች የአትሌቲክስ ማህበር (MPSSAA) ተነድፎ አሁን ባለው ማእቀፍ ለሚሠሩ ዲስትሪክቶች በትምህርት ቤቶች መካከል ስለሚደረግ አትሌቲክስ ክለሳ የተደረገበትን የሁለት ሴሚስተር መርሃግብር ካላንዳር አጽድቋል። ክለሣ በተደረገው ካላንዳር በአካል የሚጀመርበት ቀን ከፌብሩወሪ 1/2021 ወደ ዲሴምበር 7/2020 ተገፍቷል። ይህም በቀድሞው የሥራ ካላንዳር ላይ የነበሩትን በጊዜ እጥረት ምክንያት በወቅቶች መካከል ያለውን የሁለት ሣምንት መደራረብ ወቅቶችን ጨምሮ በርካታ ጉዳዮችን መፍትሄ ይሰጣል።

በ MCPS አትሌቲክስ የኮቪድ-19 ግብረሃይል፣ በአካል ወደመመለስ እና ልምምድ እና ስልጠና ላይ የተመሠረቱ እንቅስቃሴዎችን ለማድረግ በዝጅት ላይ የሚገኙ ሲሆን፥ ማሻሻያ የተደረገበት ካላንዳር ምን እንድምታ ሊኖረው እንደሚችል ገምግመው የ MCPS አመራር ውሳኔ እንዲሰጥበት አስተያየቶችን ያቀርባሉ። በተጨማሪም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ስለ ዊንተር ስፖርቶች ከ MPSSAA የተሰጡ ሃሳቦችን (ሪኮመንዴሽን) ይገመግማል።

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ከ R.A.I.S.E. Reimagined በተሰጠ ማዕቀፍ የቨርቹወል አትሌቲክስ ስራዎችን ይቀጥላል። በአካል የመመለስ እንቅስቃሴ የሚከናወነው የጤና አጠባበቅ መለኪያ መረቡ የሚፈቅድ እና ተማሪዎችን ወደ ትምህርት ቤት ከመመለስ እቅድ ጋር የሚጣጣም ከሆነ ነው።

**አገር አቀፍ የሂስፓኒክ ኮሌጅ አውደ ርዕይ ኖቬምበር 17 ቨርቹወል ይካሄዳል**

ናሽናል የሂስፓኒክ ኮሌጅ ትእይንት ማክሰኞ፣ ኖቬምበር 17 ከ 2–6 p.m. ቨርቹወል ይካሄዳል። ትእይንቱ በነጻ የሚታይ ሲሆን ለሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች እና ለወላጆቻቸው እንዲሁም ለትምህርት ቤት ካውንስለሮች ክፍት ነው።

ተማሪዎች ግባቸውን ከሚያሟሉ ኮሌጆችና ዩኒቨርስቲዎች ጋር የመገናኘት እድል ይኖራቸዋል፣ የቡድን ውይይቶችን፣ የግል ውይይቶችን እና የቪዲዮ ጭውውቶችን ከምዝገባ ካውንስለሮች ጋር ይከታተላሉ፣ እንዲሁም ከኮሌጅ እና ከዩኒቨርሲቲዎች ቨርቹወል የትእይንት ማሳያ ኪዎስክ ቪድኦችን ይመለከታሉ።

ተማሪዎች እዚህ መመዝገብ ይችላሉ። ተጨማሪ መረጃ እዚህ ይገኛል።

**ቨርቹወል የሙያ ትእይንት የ ACT-SO 2020-2021 ወቅት ሊጀመር ነው**

ናሽናል አሶሴሽን ፎር ዘ አድቫንስመንት ኦቭ ከለርድ ፒፐል (NAACP) ሞንትጎመሪ ካውንቲ ሜሪላንድ ዩኒት - የአፍሮ አካዳሚክ፣ ካልቸራል፣ ቴክኖሎጂካል፣ እና ሳይንቲፊክ ኦሊምፒክ "The Afro-Academic, Cultural, Technological, and Scientific Olympics (ACT-SO) of the National Association for the Advancement of Colored People (NAACP) Montgomery County Maryland Unit" ቅዳሜ፣ ኦክቶበር 31 እና እሑድ፣ ኖቬምበር 1 ከ 2:45 p.m. ጀምሮ የ 2020-2021 ወቅት በነፃ ACT-SO የተሰኘ ትእይንት በማቅረብ ይጀመራል። በቅድሚያ መመዝገብ አስፈላጊ ነው። በአራት የውይይት መድረኮች -- በስነጽሑፍ፣ በእንቅስቃሴ የሚታዩ ስነጥበባት፣ (ሳይንስ፥ ቴክኖሎጂ፥ እንግሊዝኛ፥ ሒሳብ)/ (STEM)፣ ንግድ እና ህዝባዊ አገልግሎት -- በመሣሰሉት የተለያዩ የሥራ መስኮች ተሰማርተው የሚገኙ ሙያተኞች ያላቸውን ኃላፊነት፣ የትምህርት ተሞክሮ እና ልዩ ልዩ የሙያ ሥራ እድሎች መኖራቸውን ተማሪዎች እንዲረዱ ያደርጋሉ።

የሙያ ትእይንቱ በዙም አማካይነት ይካሄዳል፥ እናም የእያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ አገናኝ መረብ ከታች ተዘርዝሯል፦

- ቅዳሜ፣ 10/31፦ ስነ ጽሑፍ
  2:45 PM እስከ 4:00 PM
  https://us02web.zoom.us/meeting/register/tZ0kfuihrDgsE9fMt7BlAeOS2ajFWkysB791
- ቅዳሜ፣ 10/31፦ የእይታ እና የትግበራ ስነጥበብ
  4:15 PM to 5:30 PM
  https://us02web.zoom.us/meeting/register/tZUkceuupjgpHdJZJdb4ul_nQOyNh7JrnuyD
- እሑድ፣ 11/1፦ STEM
  2:45 PM እስከ 4:00 PM
  https://us02web.zoom.us/meeting/register/tZ0qdOCpqDwpG9W8W1pGmEmKO1DSCubXKFmd
- እሑድ፣ 11/1፦ ንግድ ማቋቋምና ማካሄድ እና የማህበረሰብ አገልግሎት
  4:15 PM to 5:30 PM
  https://us02web.zoom.us/meeting/register/tZwvfu-oqDkuEt39_i_Z2_3n9E0uQDWBzJj

የመድረክ ውይይት አቅራቢዎች፦

Christopher Barclay, Photographer/Administrator, Arts on the Block

Fatmata Barrie, attorney, Senior Legislative Aide, Montgomery County Council

Stephen Bess, Poet/English professor, Montgomery College

Kelly Chauncey, Artistic Director, Unbreakable Art Foundation

Alfred L. Chester, Director of Clinical Quality and Compliance at AstraZeneca

Nancy Chiles-Shafer, Epidemiologist, Gerontologist, NIH

Rashid Darden, Award-winning writer

Matthew Goins, Entrepreneur, PUZZLE HUDDLE

Dennis Hansford, Office of Science and Technology, NOAA

Patricia Hopkins, Instrumental Music

Dr. Monique Johnson, Research Chemist, NIST

Mark Joyeux, Vocals, Director, Talent Group for Children

Vanessa Levros-Hall, International Association for Blacks in Dance

Jordan Lindsey, Journalist, Montgomery County Media

Jazmyn McKoy, Founder, Hearts of Tabitha

Rosendo Molina, Engineer

Kelsey Nelson, Digital & Broadcast Host, Washington Football Team (Clarksburg HS Alum)

**የዊንተር ኮት እርዳታ ማሰባሰብ እየተካሄደ ነው**

የቅድመ ምዋእለ ህጻናት እና የሄድስታርት ቢሮዎች በዝቅተኛ ገቢ ለሚኖሩ ተማሪዎች አዳዲስ ጃኬቶችን እርዳታ ይቀበላሉ። በተጨማሪም፥ ኮፍያዎች፣ የእጅ ጓንቶች እና የአንገት ልብሶች ጭምር ያስፈልጋሉ። ለወንዶች ወጣቶች እና ለልጃገረዶች ልክ የሚሆናቸው ቁጥር 5፣ 6፣ 6x እና 7 በኦንላይን ማዘዝ እና ቀጥሎ ባለው አድራሻ በፖስታ ቤት/UPS እንዲደርስ ማድረግ ይቻላል፦

ለ፦ ሄድ ስታርት
Rocking Horse Road Center
4910 Macon Road, Room 141
Rockville, MD 20852

አዳዲስ ጃኬቶችን በአካል ምንም ንክኪ ሳይኖር ሰኞ፣ ኖቬምበር 30 ወይም ሰኞ፣ ዲሴምበር 7 በ "Rocking Horse Road Center" በስተኋላ መኪና ማቆሚያ ቦታ ላይ ከ 9 a.m. እስከ እኩለቀን ድረስ ማቅረብ ይቻላል።

ይበልጥ መረጃ ለማግኘት፣ ለ Lisa Conlon በ lisa_w_conlon@mcpsmd.org ኢሜይል ያድርጉ

**አሜሪካ አገልግሎት የሰጡ ነገሮችን ወደፋብሪካ በመመለስ እንደገና ለአገልግሎት እንዲውሉ የማድረግ (Recycles) ቀን ክብረበዓል ኖቬምበር 13 ይካሄዳል**

በአሜሪካ አገልግሎት የሰጡ ነገሮችን በማጣራት እንደገና ለሌላ አገልግሎት እንዲውሉ የማድረግ (Recycles) ቀን አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት በዩ.ኤስ በየዓመቱ ኖቨምበር አጋማሽ ላይ አገልግሎት የሰጡ ነገሮችን አጣርቶ እንደገና ለሌላ አገልግሎት እንዲውሉ ማድረግን (recycling) ለማዳበር ስለሆነ፥ አቀናባሪዎቹ (recycling) የትምህርት ክፍለጊዜ ያካሄዳሉ። በዚህ ዓመት፣ የ "MCPS Division of Sustainability and Compliance" - የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ዘላቂነትን እና ስነ ሥርዓትን የሚያስከብር ክፍል ከሞንትጎመሪ ካውንቲ የከባቢ ጥበቃ ዲፓርትመንት ጋር በመተባበር ዓርብ ኖቨምበር 13 ክብረበዓሉን ቨርቹወል ለማካሄድ በ 4 p.m. ያከብራሉ።

ሠራተኞች፣ ተማሪዎችና ወላጆች ዙም (Zoom meeting) በመጠቀም በበዓሉ ላይ ለመሣተፍ ይችላሉ። ኩነቱ አገልግሎት የሰጡ ነገሮችን በማጣራት እንደገና ለሌላ አገልግሎት እንዲውሉ ማድረግ (recycling) ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነና ለአሜሪካ ብልጽግናና ለአካባቢ ጥበቃ ምን አስተዋጽኦ እንዳበረከተ ያብራራል።

ዙም ስብሰባ ይሳተፉ

የስብሰባ መለያ (Meeting ID)፦ 865 7591 1931
ፓስኮድ (Passcode)፦ 126295
በስልክ ለመሣተፍ፦ +1 301 715 8592